# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ጠባይ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከሴፕቴምበር 21-30/2022 የነበረው የአየር ሁኔታና ግምገማ እንዲሁም

## ከኦክቶበር 1-10 /2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2022
አዲስ አበባ

ርዕስ　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　ገፅ


እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ........ 2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት........ 3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ........ 4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር........ 4

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ........ 5

በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ........ 5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 5

እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር........ 7

ሁኔታ አዝማሚያ........ 7

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10, 2022........ 7

የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ. ........ 7

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8

እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8


## እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በሴፕቴምበር በመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር መንስኤ የሚሆኑ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከአብዛኛዎቹ የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት በመዳከማቸዉ በየጣልቃው ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተስተውሏል፡፡ ይሁን እንጂ በምዕራብ አጋማሽ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ እንዲሁም በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከሞላ ጎደል የተሻለ ጥንካሬ ተስተውሎባቸው ነበር፡፡ በሌላ በኩል ዝናቡ በተወሰኑ ደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አንፃራዊ መሻሻል እንደነበረው ተስተዉሏል፡፡ በመሆኑም አብዛኛዉ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ የሲዳማ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ የአፋር ደቡባዊ ክፍል፣ የደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ጥቂት የሰሜን ምስራቅና የምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በፉኚዶ 140.0፣ በአይራ 34.5፣ በአሶሳ፣ 35.0፣ 33.6፣ እና 37.2፣ በአየሁ 38.2፣ በብላቴ 34.5፣ በደብረታቦር 37.8፣ በደባርቅ 38.3፣ በጋምቤላ 78.6፣ በጊምቢ 40.3፣ በጎሬ 42.0፣ በሊሙ ገነት 49.3፣ በመተማ 34.0፣ በነገሌ 32.7፣ በዝዋይ 40.0፣ በወራቤ 30.6፣ በጊዳ አያና 44.4፣ 34.1 እና 41.9፣ በቡሬ 36.6 እንዲሁም በእምድብር 36.2 በሚ.ሜ ይገኙባቸዋል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በትግራይና አማራ ክልሎች ዞኖች፣ በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ በሁሉም የወለጋና ሸዋ ዞኖች፣ በቡኖ በደሌ፣ በኢሉ አባቦራ፣ በጅማ፣ በአርሲና ምዕራብ አርሲ፣ በባሌና ምስራቅ ባሌ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በሀላባ፣ በከምባታ ጠምባሮና ዳዉሮ ዞኖች፣ በጉጂና ምዕራብ ጉጂ እና በሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ25-184 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በአፋር፣ በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደቡባዊው ክፍል፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሁሉም ዞኖች፣ በሲቲና ፋፈን ዞኖች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ 4 ላነሱ ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር የምዕራብ ትግራይ፣ አብዛኛው አማራ፤ ቤንሻንጉል ጉምዝ፤ የጋምቤላ ሰሜናዊው ክፍል፤ አብዛኛው የኦሮሚ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በጎፋና በደቡብ ኦሞ እንዲሁም በደቡብ አፋር ክልል ሁሉም ዞኖች ላይ በድሬዳዋና ሀረሪ እንዲሁም በአዲስ አበባ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ የሰሜን አፋር ክልል፣ ሁሉም የሶማሌ እንዲሁም የደቡብ ጋምቤላ ዞኖች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3)


ካርታ 1   እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3   ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች   መደበኛ   ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከሴፐቴምበር 21 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሴፐቴምበር ወር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት በምዕራብ አጋማሽ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ እንዲሁም በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአመዛኙ እርጥበታማ ሁኔታ ተጠናክሮ እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተለይም አብዛኛዉ አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ፣ የሲዳማ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ የአፋር ደቡባዊ ክፍል፣ የደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና ጥቂት የሰሜን ምስራቅና የምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ እድገታቸውን ላልጨረሱና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን ውኃ ከማቅረብ አንጻር እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ ምንም እንኳን እርጥበቱ ከሰሜንና ከሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ ቀንሶ የተስተዋለ ቢሆንም፤ በአንጻራዊ መልኩ ባለፉት የክረምት ወራት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅ ለነበሩትና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ደቡባዊ ክፍል በመጠኑም ቢሆን የእርጥበት ሁኔታቸው እንደተሻሻለ የተሰበሰቡና የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ በአካባቢዎቹ የነበረውን ደረቅ ሁኔታ ከማስታገስና ከማሻሻሉም በተጨማሪ በደቡብ የሀገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርና የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና እንደነበረው ነው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4   እ.ኤ.አ ከሴፐቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከ 21-30 ሴፕቴምበር 2022 በአብዛኛው የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ ገፅታ ነበረው፡፡ በዚሁ መሰረትም አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ተከዜ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ስምጥሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ የላይኛው አዋሽ፣ ዋቢሸበሌ እና በጥቂት የአፋር ደናክል ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪ በአብዛኛው አዋሽ፣ በመካከለኛው አፋር ደናክል እና በመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም በታችኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመጪዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህም መሰረት ቀደም ብሎ የጀመረው የክረምት ወቅት ዝናብ በምዕራብ አጋማሽ ላይ የሚቀጥል ሲሆን፣ በተጨማሪም በጥቂት በደቡብና በምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በተወሰነ መልኩ ሊጨምር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በዚህም መሰረት በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፤ ፀሀያማው የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፣ አልፎ አልፎም ከሚፈጠሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በተለያዩ ቦታዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ አርሲና ባሌ፣ የጉጂ ዞኖች፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ ጎንደር ዞኖች፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ እንዲሁም የባህር ዳር ዙሪያ እና አገው አዊ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ ከደቡብ ኦሞ እና ከኮንሶ ዞኖች በስተቀር ሁሉም የክልሉ ዞኖች፤ የሲዳማ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዞኖች፤ በአብዛኛው ከመደበኛ ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በሰሜንና በመካከለኛዉ ጎንደር እንዲሁም በምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ በምስራቅ ባሌ በጥቂት የቦረና ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የመካከለኛዉና የምስራቅና የደቡብ ዞኖች፤ አዲስ አባባ፣ ጋምቤላ፤ አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች በመነሳት አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10, 2022
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ.

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የኦክቶበር የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት በአብዛኛው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ገጽታ ይኖራል፡፡ በመሆኑም የመኸር ሰብል አምራች በሆኑትም ሆነ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የእርጥበት ሁኔታው ከቀደመው አንጻር ሲታይ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ጥንካሬ ይዘው ሊቀጥሉ እንደሚችሉና በተለይም ዝናቡ በምዕራባዊው አጋማሽ በተጨማሪም ወደ ደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት እንደሚኖራቸው ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቀጣይ ለሚያከናውኑት የግብርና ስራ እንቅስቃሴዎች በጎ ጎን ይኖረዋል። የመኸር ሰብል ሰብል አብቃይ ቦታዎችም ላይ ዘግይተው ለተዘሩና እድገታቸውን ላልጨረሱ እንዲሁም በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት በተጨማሪም በዚህ ጊዜ የእርጥበት ሁኔታው ወደ ደቡብ የሚያደርገው መስፋፋት ወቅታዊ እርጥበት ማግኘት በሚጀምሩት በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ደጋማ አካባቢ ላይ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር እና በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዕ ይኖረዋል። በሌላ በኩል ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡ እንዲሁም በዚህ ጊዜ በመደበኛ ሁኔታ የሰብል ስብሰባ በሚካሄድባቸው በሰሜናዊ አጋማሽም ሆነ በአንዳንድ ቆላማ አካባቢዎች ላይ ሊኖር የሚችለው ደረቅ ሁኔታ ለሰብል ስብሰባ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ በባሮአኮቦ፣ አባይ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው አዋሽ፣ ዋቢሸበሌና የገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው አዋሽ፣ ምስራቃዊ አባይ፣ የታችኛው ገናሌዳዋ፣ ስምጥሸለቆ፣ የታችኛው ባሮአኮቦ እና የመካከለኛው እና የታችኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች መጠነኛ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡